ያቀናሉ፣ ወይነብሩ፡ ውስቴታ፡ ተሐንፀ፡ ቤተ፡ ወኢትነብሩ፡ ብሎ፡ ነበርና፡ በኢየሩሳሌም፡ ጠላት፡ ጠፍቶላቸው፡ ተዘል ሰው፡ ይኖራሉ፤

ወይተክሉ፡ ወይነ፡ ወይሰትዩ፡ ወይኖሙ፣

ትተክሉ፡ ወይነ፡ ወኢትሰትዩ፡ ብሎ፡ ነበርና፣ ወይኑን፡ ይተ ክላሉ፣ ይጠጣሉ፣

ወይተክሉ፡ አዕፃዳተ፡ አቅማሕ፡ ወይ በልዑ፡ ፍሬሁ፣

ተክል፡ በሚተክሉበት፡ ቦታ፡ ሁሉ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡ ተክል፡ ይተክላሉ፣ ፍሬውን፡ ይበላሉ፤

፲፭፤ ወእተክሎሙ፡ ውስተ፡ ምድሮሙ፣

በሀገራቸው፡ አጸናቸዋለሁ፤

ወአልቦ፡ እንከ፡ ዘየወጽኦሙ፡ እምድ ሮሙ፡ እንተ፡ ወሀብክዎሙ፡ አነ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፣

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እኔ፡ ከሰጠኋቸው፡ አገር፡ የሚ ያስወጣቸው፡ የለም አለ፤

ተፈጸመ፡ ዘአሞጽ፡ ነቢይ፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ ትኩን፡ ምስሌነ፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፣

ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግባው፡ አሜን፡፡

# ዘሚክያስ ነቢይ

## መቅድም

ሚክያስ፡ ማለት፡ መኑ፡ ከማከ፡ መኑ፡ ከመ፡ እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነው፤ ትውልዱ፡ ከነገደ፡ ብንያም፡ ነው፤

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀበ፡ ሚክያስ፡ ነቢይ፡ ወልደ፡ ሞራት፣

ዘመጽአ፡ ዘተነግረ፡ ሲል፡ ነው፤ ለሞራት፡ ልጅ፡ ከሚክያስ፡ ዘንድ፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚ አብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤

በመዋዕለ፡ ያገዩን፡ ወኢዮአታም፡ ወአ ካዝ፡ ወሕዝቅያስ፡ ነገሥተ፡ ይሁዳ፣

እለ፡ ነግሡ፡ በይሁዳ፣ እለ፡ ነግሡ፡ ለይሁዳ፡ ይላል፣ በይ ሁዳ፡ በነገሡ፡ በነዚህ፡ ዘመን፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብ ሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ ስለ ምን፡ እነዚህን፡ አነሣቸው፡ ቢሉ፣ በነዚህ፡ ዘመን፡ ብመክ ራቸው፡ ባስተምራቸው፡ አንሰ ማም፡ ብለው፡ ጠፉ፡ ለማለት፤

ዘርእየ፡ በእንተ፡ ሰማርያ፣

ሰማርያ፡ እንድትጠፋ፡ ዓይቶ፤

ወበእንተ፡ ኢየሩሳሌም፣

ኢየሩሳሌምም፡ እንድትጠፋ፡ ዓይቶ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ አንድም፡ አሥሩ፡ ነገድ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ እንዲማረኩ፡ ዓይቶ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ ነው፤

፪፤ ስምዑ፡ አሕዛብ፣

አሕዛብ፡ ስሙ፤

ወታፅምዕ፡ ምድር፣

ምድርም፡ ትስማ፡ ማለት፡ የተ ከሉባትን፡ አታጽድቅ፡ የዘሩባ ትን፡ አታብቅል፤

ወኵሎሙ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ውስቴታ፣

በውስጧ የሚኖሩ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ይስሙ፤

ወይከውነክሙ፡ እግዚአብሔር፡ ሰማዕተክሙ፣

አንሰማም፡ ብትሉ፡ እግዚአብ ሔር፡ ምስክር፡ ይሆንባችኋል፤

www.ethiopianorthodox.org

ወለኢየሩሳሌምኒ፡ በዓመፃ፤

ኢየሩሳሌምን፡ በግፍ፡ የምትሠሯት፡ ስሙ፤

፲፩፤ መኳንንቲሃኒ፡ በሕልያን፡ ይኳንኑ፤

መኳንንቱ፡ መማለጃ፡ ተቀብለው፡ ይፈርዳሉ፤

ወካህናቲሃኒ፡ በዓስብ፡ ያወሥዑ፤

ካህናቱም፡ ዋጋ፡ ተቀብለው፡ ያስተምራሉ፤

ወነቢያቲሃኒ፡ በወርቅ፡ ያስግሉ፤

ነቢያቶችዋም፡ ወርቅ፡ ተቀብለው፡ ይጠነቍላሉ፤

ወላዕለ፡ እግዚአብሔር፡ ያሰምኩ፤

እንዲህ፡ እያደረጉ፡ እግዚአብሔር፡ አድሮብናል፡ በእግዚአብሔር፡ አመንን፡ ይላሉ፤

ወይብሉ፡ አኮኑ፡ እግዚአብሔር፡ ምስሌነ፡ ወኢይረክበነ፡ እኩይ፤

እግዚአብሔር፡ ከኛ፡ ጋር፡ ያለ፡ አይደለምን፡ መከራ፡ አያገኝንም፡ ይላሉ፤

፲፪፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ በበይነ፡ ዚአክሙ፡ የሐርስዋ፡ ለጽዮን፡ ከመ፡ ገራህት፤

በእንተ፡ ዝንቱና፡ በበይነ፡ ዚአክሙ፡ አንድ፡ ወገን፤ ስለዚህ፡ ነገር፡ በናንተ፡ ኃጢአት፡ ምክንያት፡ ጽዮንን፡ እንደ እርሻ፡ ያርሷታል፤ ጎንደር፡ ይታረስ፡ እንዲሉ፤ አንድም፡ በዳዊት፤ በሰሎሞን፡ መቃብር፡ ወርቅ፡ እንደተገኘ፡ ወርቅ፡ እናገኛለን፡ ብለው፤

ወትከውን፡ ኢየሩሳሌም፡ ከመ፡ ልገተ፡ ዓቃቤ፡ ቀምሕ፤

ኢየሩሳሌም፡ እንደፍሬ፡ ጠባቂ፡ ጎጆ፡ ትሆናለች፤

ወደብረ፡ ቤቱሂ፡ ከመ፡ ዖመ፡ ገዳም፤

አምስቱ፡ ቆመ፡ ብእሲ፡ ስድስቱ፡ ቆመ፡ ብእሲ፡ ሰባቱ፡ ቆመ፡ ብእሲ፡ ምድረ፡ በዳ፡ ይሆናል።

## ምዕራፍ ፬

፩፤ ወይከውን፡ በደኅሪ፡ መዋዕል፤

በሕዝቅያስ፡ ዘመን፡ እንዲህ፡ ይሆናል፤

ያስተርኢ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ድልው፡ ውስተ፡ አርእስተ፡ አድባር፡ ወይትሌዓል፡ መልዕልተ፡ አውግር፤

ይከውን፡ ያለውን፡ ያስተርኢ፡ ብሎ፡ አመጣው፤ በሕዝቅያስ፡ ጊዜ፡ ቤተ፡ መቅደስ፤ በኪዳነ፡ አብርሃም፤ በኪዳነ፡ ይስሐቅ፤ በኪዳነ፡ ያዕቆብ፡ ጸንቶ፡



ይታያል፤ በዘሩባቤል፡ ጊዜ፡ ቢሉ፡ ባምስቱ፤ በስድስቱ፤ በሰባቱ ቆመ፡ ብእሲ፡ ጸንቶ፡ ይታያል፤

፪፤ ወየሐውሩ፡ ብዙኃን፡ አሕዛብ፤

ብዙ፡ አሕዛብ፡ ወደ፡ ቤተ፡ መቅደስ፡ ይሄዳሉ፤

ወይብሉ፡ ንዑ፡ ንዕርግ፡ ውስተ፡ ደብረ፡ እግዚአብሔር፤

ከመሄዳቸው፡ አስቀድመው፡ ኑ፡ ወደቤተ፡ እግዚአብሔር፡ እንሒድ፡ ይላሉ፤

ወውስተ፡ ቤተ፡ አምላከ፡ ያዕቆብ፤

ወደያዕቆብ፡ ፈጣሪ፡ ማደሪያ፡ ወደቤተ፡ መቅደስ፡ እንሂድ፡ ይላሉ፤

ይንግሩነ፡ ፍኖቶ፡ ወንሑር፡ በዓሠሩ፤

ዘጠኙን፡ ቃላት፡ ያስተምሩን፡ ዘንድ፡ በኢታምልክም፡ ጸንተን፡ እንኖር፡ ዘንድ፡ ኢታምልክን፡ ዐሠር፡ አላት፤ ፍለጋ፡ ከሀገር፡ ከመንደር፡ እንዲያደርስ፡ ኢታምልክም፡ ከዘጠኙ፡ ቃላት፡ ታደርሳለችና፤ ይንግሩነ፡ ፍኖቶ፡ ወዓሠሮ፤ ኢታምልክን፡ ዘጠኙን፡ ቃላት፡ ይነግሩን፡ ዘንድ፤ አንድም፡ ንሑር፡ በዓሠሩ፡ ወበፍኖቱ፡ ይላል፤ በኢታምልክ፡ በዘጠኙ፡ ቃላት፡ ጸንተን፡ እንኖር፡ ዘንድ፤

እስመ፡ እምጽዮን፡ ይወጽእ፡ ሕግ፡ ወቃለ፡ እግዚአብሔር፡ እምኢየሩሳሌም፤

ከነቢያት፡ ትንቢት፡ ከካህናት፡ ትምህርት፡ ይገኛልና፤ አንድም፡ ከነቢያት፡ ትንቢት፤ ከካህናት፡ ትምህርት፡ ይገኛልና፤ ኑ፡ ወደቤተ፡ እግዚአብሔር፡ እንሂድ፡ ይላሉ፡ ይላል፡ ነቢዩ፤ አንድም፡ ወይከውን፡ በደኃሪ፡ መዋዕል፡ ብለህ፡ መልስ፤ በዘመነ፡ ሐዲስ፡ በጌታ፡ ጊዜ፡ እንዲህ፡ ይሆናል፤ በወርቅ፡ በብር፡ ከተሠራ፡ ከነገሥታቱ፡ ቤት፡ በኖራ፡ በጭቃ፡ የተሠራ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ በማዕርግ፡ በልጦ፡ ይታያል፤ ወደቤተ፡ ክርስቲያን፡ ከመሄዳቸው፡ አስቀድሞ፡ ኑ፡ ወደቤተ፡ ክርስቲያን፡ እንሂድ፡ ይላሉ፤ ዘጠኙን፡ ቃላት፡ ኢታምልክን፡ ይነግሩን፡ ዘንድ፤ በሕገ፡ ወንጌልም፡ ጸንተን፡ እንኖር፡ ዘንድ፡ ሕግ፡ ጌታ፡ ከእመቤታችን፡ ይወለዳ

www.ethiopianorthodox.org

ልና፤ አንሰሰወት፡ ሕግ፡ ወእስ ተርእየት፡ ውስተ፡ ዓለም እን ዲል፤ አንድም፡ ሐጋጌ፡ ሕግ፡ ጌታ፡ ከእመቤታችን፡ ተወልዷ ልና፡ ጽዮን፡ አላት፤ ፀወነ፡ ሥጋ፤ ፀወነ፡ ነፍስ፡ ናትና፤ አካላዊ፡ ቃል፡ እርሱ፡ ከእመ ቤታችን፡ ተወልዷልና፤ ኢየሩ ሳሌም፡ እንጂ፡ ማለት፡ መካነ፡ ሰላም፡ ማለት፡ ነው፤ እሷ ንም፡ ብኪ፡ ድኅነ፡ ዓለም፡ ወበ ወልድኪ፡ ኮነ፡ ሰላም፡ ይላታ ልና፤ አንድም፡ ሕግ፡ ወንጌል፡ በቤተ፡ ክርስቲያን፡ ይነገራልና፤ አካላዊ፡ ቃል፡ እርሱ፡ በሥ ጋነት፡ በደምነት፡ በቤተ፡ ክር ስቲያን፡ ይገኛልና፡ ወደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ እንሂድ፡ ይላሉ፤

፫፤ ወይኴንን፡ በማዕከለ፡ አሕዛብ፤

ዘሩባቤል፡ በአሕዛብ፡ መካከል፡ ይፈርዳል፤

ወይዛለፎሙ፡ ለአሕዛብ፡ ጽኑዓን፡ እስከ፡ ነዋኃት፡ አድባር፡ ወብሔር፤

ጽንፍ፡ እስከ፡ ጽንፍ ያሉ፡ ጽኑዓን፡ አሕዛብን፡ ብትገብሩ፡ ገብሩ፡ ያለዚያ፡ እወጋችኋ ለሁ፡ እያለ፡ ይዘልፋቸዋል፤

ወይመትሩ፡ ኵያንዊሆሙ፡ ለምሳር፤

ጦራቸውን፡ ምሳር፡ አድርገው፡ ይጨፈልቁታል፤

ወአስይፍቲሆሙ፡ ለማዕፀድ፤

ሰይፋቸውን፡ ማጭድ፡ አድር ገው፡ ያሠሩታል፤

ወኢያነሥኡ፡ እንከ፡ ሕዝብ፡ ዲበ፡ ሕዝብ፡ መጥባሕተ፤

አንዱ፡ በአንዱ፡ ላይ፡ ጦር፡ አያ ነሣም፡ ዘመኑ፡ ዘመነ፡ ሰላም፡ ሆኖ፤ ይበልዑ፡ ወይሰትዩ፡ ታሕተ፡ ወይኖሙ፡ ወበለሶሙ፡ ወይነብሩ፡ ተአሚኖሙ፡ እን ዲል፤ ጠላት፡ ጠፍቶላቸው፡ አርፈው፡ ይኖራሉ፤

ወኢይትሜሀሩ፡ እንከ፡ ቀትለ፤

ሰልፍ፡ አይማሩም፤ ሰልፍ፡ መማር፡ አለና፤ በፈረስ፡ እየ ጋለቡ፡ የአንዱን፡ እግር፡ ሰና ፊል፡ በአንድ፡ እግር፡ ማግ ባት፤ በአረቂ፡ መርፌ፡ ፈትል፡ ማግባት፤ ዘንግ፡ ወርውሮ፡ መቅለም፤ አለንጋ፡ ማንሳት፡ አለና፤ አንድም፡ ወይኴንን፡ ማዕከለ፡ አሕዛብ፡ ብለህ፡ መልስ፤ ጌታ፡ በአሕዛብ፡ መካ ከል፡ ተሐድገ፡ ለኪ፡ ኃጢአ ትኪ፡ ፈቀድኩ፡ ንጹሕ፤ ተን ሥእ፡ ንሣእ፡ አራተከ፡ እያለ፡



ይፈርዳል፤ ጸሐፍት፡ ፈሪሳው ያንን፡ አሌ፡ ለክሙ፡ ጸሐፍት፡ ፈሪሳውያን፡ መደልዋን፡ እያለ፡ ይዘልፋቸዋል፤ ጦራቸውን፡ መቆፈሪያ፡ አድርገው፡ ያሠሩ ታል፤ ሰይፋቸውንም፡ ሠቅ፡ መስቀል፡ አድርገው፡ ያሠሩ ታል፤ አንዱ፡ በአንዱ፡ ላይ፡ ጠብ፡ አያነሳም፤ ዘመኑ፡ ዘመነ፡ ሰላም፡ ሆኖ፤ ወያጠ ፍዕ፡ ሠረገላ፡ እምኤፍሬም፡ ወአፍራሰ፡ እምይሁዳ፡ ወይከ ውን፡ ሰላም፡ በመዋዕሊሁ፡ እንዲል፡ ሰልፍ፡ አይማሩም፤ ሐተታው፡ እንዳለፈው፡ ነው፤

፬፤ ወየአርፉ፡ ኵሎሙ፡ ታሕተ፡ ወይኖሙ፡ ወበለሶሙ፤

ከወይኑ፡ ከበለሱ፡ ሥር፡ አር ፈው፡ ይኖራሉ፤

ወአልቦ፡ ዘይጌርሞሙ፤

የሚያስፈራቸው፡ የለም፤

እስመ፡ አፉሁ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፡ ነበበ፡ ከመዝ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ተናግሯልና፤

፭፤ እስመ፡ ኵሎሙ፡ አሕዛብ፡ የሐውሩ፡ በፍኖቶሙ፤

አሕዛብ፡ በኃጢአታቸው፡ ጸን ተው፡ የሚኖሩ፡ ስለሆኑ፤

ወንሕነሰ፡ ነሐውር፡ በስመ፡ እግዚአ ብሔር፡ አምላክነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም፤

እኛ፡ ግን፡ ለዘለዓለሙ፡ በእግዚ አብሔር፡ አምነን፡ እንኖራለን፤

፮፤ ወዓዲ፡ ይእተ፡ አሚረ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፤

ዳግመኛ፡ ያን፡ ጊዜ፡ እግዚአብ ሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

አስተጋብኦ፡ ለዝሩት፤

ሁለቱን፡ ነገድ፡ እሰበስባ ቸዋለሁ፤

ወእትዌከፋ፡ ለግድፍት፡ ለእንተ፡ አርኃቅዋ፤

ብዙ፡ ዘመን፡ ያራቅኋት፤ በመ ከራ፡ የጣልኋት፡ ዐሥሩን፡ ነገድ፡ በረድኤት፡ እቀበላታለሁ፤ እንዲህ፡ ስላለ፡ ግን፡ በግድ ፍት፡ ዝሩት፤ በዝሩት፡ ግድ ፍት፡ ያለበት፡ ነው፤

፯፤ ወእሬስያ፡ ለዝሩት፡ ትርፍተ፤ ወለግድፍት፡ ሕዝበ፡ ጽንዕተ፤

ሁለቱን፡ ነገድ፡ ብዙ፡ አደርጋ ታለሁ፤ በመከራ፡ የጣልኋት፡ አሥሩን፡ ነገድ፡ አጸናታለሁ፤

ወይነግሥ ሎሙ፡ እግዚአብሔር፡ በደ ብረ፡ ጽዮን፡ እምይእዜ፡ ወእስከ፡ ለዓለም፤

ከዛሬ፡ ጀምሮ፡ እግዚአብሔር፡ ለዘላለሙ፡ በደብረ፡ ጽዮን፡

www.ethiopianorthodox.org

